# ደንጋይ ብርጭቆ…

እንደ ተአምር ተመልክተነው
ከእጅ-እጅም ተቀባብለነው
‘ግሩም፣ ዕጹብ ነው፣ የሚደንቅ ዕቃ
‘ከቶ አይሰበር፣ ወይም አይነቃ!’
እያልን ከላይ፣ ከደረጃው
እያንከባለልን ስናንጃጃው፣
ተረኛው ልጅም ይሯሯጥና
አንስቶት ቶሎ ያመጣውና
ከላይ ጀምሮ ይለቅቀዋል…
ደግሞ፣ ደጋግም ያንቋቋዋል።





የሚገርምና የሚደንቀው
ለማመን ከቶ የሚጨንቀው
እየተላጋ ወርዶ፣ ተዋርዶ
ስፈሩን ሁሉ አንጐዳጉዶ
ደረጃውንም እንደ ጨርሰ፤
‘ከስሚንቶው ላይ ተከስከሰ…
‘አበቃለት፣ ጉድ ሆነ!’ ስንል
በጤናው ሄዶ ከመንከባለል
አይሸራረፍ፣ አይሰበር!
አይሰነጠቅ፣ አይቧጨር።
እንዲህ እያልን በልጅነት
ደንጋይ ብርጭቆን አፌዝንበት…

አንድ ቀን ታድያ በወግ፣ በደምቡ፣
ሻይ ሲቀዱ ፈነዳ ቦምቡ!
ምን አስማቱ ነው፣ እኮ ምን መጣ?
አስመርሮታል የግዚሃር ቁጣ…

መሸረፍ አለ፣ ብሎም መሰንጠቅ
ከሁለትና ከሦስት መፋረቅ፣
ሰምተንም አናውቅ እንደዚያ መብረቅ!
እንደ አሸዋ ጭራሹን መድቀቅ…
ብትንትን ብሎ እንደ በረዶ
ተዘራው እንጂ ከመሬት ወርዶ!
ለካስ ለብዙ ዘመን ያን ጉዱ
ሲያብላላው ኖሯል ቂሙን በሆዱ።



ገ/ኢ. ጐርፉ።